# የሊል (ፈረንሳይ) «የአለም ዜጎች ጉባኤ»

## ይኸኛው አልሰራም!! ሌላ አይነት ዓለም ይቻላል?

በአሁኑ ወቅት አለማችንን ወደ ጥፋት ይዘው ሊነጉዱ የሚችሉ ሶስት ዋና ዋና መዛባቶች አሉ። አንደኛው በበለጸጉት አገሮችና ባልበለጸጉት አገሮችመሃከል እየሰፋ የሚሄደው አለመመጣጠን። ሁለተኛ በሀገሮች በራሳቸው ውስጥ በዜጎች መሃከል እየሰፋ በመሄድ ላይ ያለው የሃብትና የኑሮ ደረጃ አለመመጣጠን። ሶስተኛ ስለ ነገ ግድ የሌለው ቅጥ ያጣ የምርት ማሳደግና የገንዘብ ማካበት እሽቅድድም ላይ ያተኮረው «የእድገት»አቅጣጫ እየፈጠረ ያለውየተፈጥሮና የአካባቢ መውድምና መበከል። እነዚህ ባለሶስት ፈርጅ ቀውሶችበአንድነትና በአንድ ሂደት የሚፈቱበት ሁኔታ ካልተመቻቸ በሚቀጥለው ክፍለዘመን አለምንና የሰውን ዘር ወደ ጥፋት ይዘው ሊነጉዱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። ሃያ አንደኛው ክፍለዘመን የሰው ልጅና የአለማችን መልሚያ እንጂ የመጥፊያ ክፍለዘመን እንዳይሆን ከተፈለገእነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ መልክና እቅድ ባለው ሁኔታ በአለም አቀፍ ደረጃ ከወዲሁ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ዛሬ ከነዚህ አስደንጋጭ ሃቆች በመነሳት በመላው አለም ያለውን አካሄድ ከጥያቄ ውስጥ አስገብተው የአቅጣጫ ለውጥ እንዲደረግ የሚታገሉ ሃይሎች እየተበራከቱ ይገኛሉ። ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ወዲህ በመተከል ላይ ያለው ግሎባላይዜሽን በሚል ስም የሚታወቀው ስርአት እነዚህን ቀውሶች ከማረም ይልቅ የሚያባብስ ሆኖ በመገኘቱ ከጥቂትአመታት ወዲህ ይህንን አውዳሚ አለም አቀፍ ሂደት በመቃወም «ሌላ አይነት ግሎባላይዜሽን» በሚል መፈክር እሱም እንደሚዋጋው ስርአት በአለም አቀፍ ደረጃ እየተቀናጀ ከእለት እለት እየሰፋ፣ ከእለት እለት እለት አማራጭ የሚለውን መፍትሄና አቅጣጫ መልክ ባለው ሁኔታ እየነደፈ በመሄድ ላይ እንቅስቃሴ በመከሰት ላይ ይገኛል።

እኛና ህዝባችን በእላት ከእለት ችግሮች እየተዋከብን ስለምንገኝ፣ዘልአለማችንን በአስቸኩዋይ ሁኔታዎች ውስጥ ስላለን፣ እንኩዋን ስለመጭው ክፍለዘመን የአለም ሁኔታ ቀርቶ የዛሬ አመት የራሳችን፣ የቤተሰባችን፣ የመንደራችንና የአገራችን እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ እንኩዋን ስለሌለን እዚህ አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተገቢ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችል ራእዩም፣ ፋታውም ያለን አይመስልም። አስፈላጊነቱም አይታየን።

ያለው ትልቅ ፓራዶክስ እዚህ ላይ ነው። እርግጥ በዚህ አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ በተለይ በደቡብ አሜሪካና ባንዳንድ አውሮፓ አገሮች ገበሬዎችን የሚጨምር ሰፋፊ እንቅስቃሴ ይታያል። ነገር ግን በግንባርቀደምነት የሚታገሉት ሃይሎች በአብዛኛው እስከዚህምበዛሬው ችግራቸው ሳይሆን የአለም ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ የዛሬ ሃያ ሰላሳ አምሳ መቶ አመት ሊመጣ የሚችለውን ጥፋት መዝነው «ይህንን አንቀበለውም» በማለት የተነሳሱ ሃይሎች ናቸው።

እኛስ? ልብ አላልነውም እንጂ የሚያገባን አይመስለንም እንጂ እኛ ከዛሬው የዚህ ሁኔታ ገፈት ቀማሽ ሰለባ ነን።

ሶስቱ መዛባቶች ምንም ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ ተያይዘውና ተጋግዘው ከማንም ይበልጥ ከሰውነት ውጭ እያደረጉን ያሉት እኛን ነው። በሃገሮች መሃከል እየሰፋ የሚሄድ የሃብት አለመመጣጠን ሲባል በመደህየት ላይ ያለችውን የኛን አገር ይመለከታታል። በየሃገሩበዜጎች መሃከል አስከፊ የሆነ የሃብትና የኑሮ ደረጃ አለመመጣጠን የሚባለውንም በተለይ ከአስር አመታት ወዲህ «ነጻ ገበያ» በሚባለው ፈሊጥ አማካኝነት ቁጥራቸው በየቀኑ እየጨመረ የሚሄድ ሚልዮኖች ክፋቱ በየእለቱ በሚጨምር ሁኔታ ከሰውነት ደረጃ እየወጡ ጥቂቶች ደግሞ ከሃብታም አገሮች ሃብታሞች የማይተናነስ ሰማይ ጠቀስ ሃብት እያካበቱ የገነት ደሴቶች ውስጥ ሲኖሩ እናያለን። የተፈጥሮና የአካባቢ ውድመትና ብክለት ሲባልምከማንም ይልቅ ይመለከተናል። በበለጸጉት አገሮች የተከለከሉ ኬሚካሎችና «ማዳበሪያ» ተብየ ነገሮች በጥቂት ስግብግብ ድንበር ዘለል ኩባንያዎችና አገር በቀል አት

ራፊዎች ወደሃገራችን እየገቡ፣ ለድሃው ገበሬ በውድ ዋጋ እየተሸጡ እሱን ለእዳ ምድራችንንም ለውድመት እየዳረጉ በሃገራችን «የርሃብ ዘሮች» በመዘራት ላይ ባሉበት ሁኔታ፣ ደኖቻችን እየጋዩ ሰሞኑን «ኢትዮጵያ በኢኮሎጅካል ውድመት አፋፍ ላይ ነች» የሚል ማስጠንቀቂያ ተመድ አው ጥቶ ስናይ በተፈጥሮና በሰው ዘር መሃከል እየሰፋ መጣ የሚባለው አደገኛ መዛባት እኛን አይመለከ ተንም ማለት አይቻልም። በድሃ አገሮች ላይ ድሮውንም ቢሆን ሙሰኛና አፋኝ መንግስታት ለራሳ ቸው እንጂ ለህዝብ ጥቅም አልተበደሩትም በሚል መነሾ የድሃ አገሮች እዳ ሙሉ በሙሉ ይሰረ ዝ ሲባል ይህ ትግል በየአመቱ ከኤክስፖርት ከሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ግማሹን ለእዳና ለወለድ ክፍያ የምታውለውን ሃገራችንን አይመለከታትም ማለት አይቻልም። ይህ ሁሉ ከማንም ባላነሰ ይ መለከተናል።

ሌላም ጉዳይ አለ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደታዘብነው ከሆነ አልፎ አልፎ አንዳንድ ወገኖ ች ይህንን የግሎባላይዜሽን ጉዳይ ሲያነሱ፣ የሃገር ሉአላዊነት ሲሉ፣ ያለውን አለም አቀፋዊ ስርአ ት የመቃወም ፍንጭ ሲያሳዩ ባንዳንድ አካባቢዎች «የተቀየረው አለም አቀፍ ሁኔታ ያልገባቸው የ ድሮ ሰዎች» አንዳንዴ እንደውም «አክራሪዎች» እየተባሉ ሲፈረጁ ታዝበናል። ዛሬ ይህንን ግፈኛ ስርአት ለመቃወም ባሜሪካ፣ በአውሮፓ፤ ባፍሪካና በእስያ እየተነሳሳ ያለው እንቅስቃሴ የጥቂት አ ክራሪዎች መፍጨርጨር ሳይሆን ቀስ በቀስ ሚሊዮኖችን እያሳተፈ በመሄድ ላይ ያለ ሰፊ አለም አ ቀፍ ህዝባዊ እንቅስቃሴ መሆኑን እያስመሰከረ ነው። ከዚህ እንቅስቃሴና ያለው ስርአት በማባባስ ላ ይ ካለው አደገኛ መዛባት አንጻር ሲታይ በኛ ግምት የአለም ሁኔታ ያልገባቸው አዲሱን ስርአት አ ይናችንን ጨፍነን እንቀበል የሚሉት እንጂ አማራጭ ይፈለግ የሚሉት ሃይሎች እንዳልሆኑ ዛሬ ባ ይሆን በመጭው አጭር ጊዜ ግልጽ እንደሚሆን ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

በአለም አቀፍ ደረጃ በመነሳሳት ላይ ያለው ጸረ ግሎባላይዜሽን እንቅስቃሴ እነዚህንዛሬ አገ ራችንን በማውደም፣ህብረተሰባችንን በማዝረክረክ፣ ህዝባችንን ከሰውነት ውጭ በማድረግ ያሉትን መዛባቶች የሚቃወም እንቅስቃሴ ነው። ያገባናል ብለው በመንቀሳቀስ ላይያሉት የአለም ዜጎች ይ ችን ምድር ለቀጣይ ትውልዶች ሃላፊነት በሚሰማው መንፈስ ለሚንከባከብ፣ እርስበእርስ በመተጋገ ዝ አላማ ለሚራመድ፣ የሃይማኖት፣ የቋዋንቋዋ፣ የባህል ልዩነቶችን እንደእንቅፋት ሳይሆን እንደጸ ጋ ለሚያከብርና ለሚንከባከብ የሚያስችል «ሌላ አይነት ግሎባላይዜሽን» የመገንባት ራእይ አንግበ ው የሚንቀሳቀሱ ዜጎች ናቸው።

በዚህ መልክ እየተነሳሳ ካለው አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ መሃከል ከህዳር 20 እስከ30 ቀን 1994 ዓ.ም. በፈረንሳይ አገር ሊል በተባለች ከተማ የተካሄደውን «የአለም ዜጎች ጉባኤ» በሚል ስ ም የታወቀውን ሰፊ ስብሰባ ያዘጋጀው «ሃላፊነት ለሚሰማት፣ ለምትተጋገዝና ስብጥርጥርነቱዋን ለ ምትንከባከብ አለም የተቋዋቋዋመ አልያንስ» በሚል ስም ከስምንት አመታት በፊት ተቋዋቁሞ ባሁ ኑ ወቅት በመላ አለም ዜጎች የሚያሳትፉበት ሰፊ እንቅስቃሴ ይገኝበታል።

በዚህ አልያንስ በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያዊ ምሁራንንና የሲቢክ ማህበራት መሪዎችን ጨምሮ ካራት መቶ በላይ የሚሆኑ ከሁሉም አህጉሮች ከመቶ አስራ አምስት አገሮች በላይ የመ ጡ ተሳታፊዎች ተገኝተው ነበር። ስብሰባው በአዘገጃጀቱ ከሌሎች እንደዚህ አይነት ስብሰባዎች ሁሉ ለየት ያለ ነበር። ከወዲሁ በአዘጋጆቹ የተነደፈና በተሳታፊዎቹ ላይ የተጫነ አጀንዳ አልነበረ ውም። እርግጥ አልያንሱ ከፍ ብለን ከጠቀስናቸውና አዲሱ የግሎባላይዜሽን ስርአት እያባባሳቸው ከሄዱት አደገኛ መዛባቶች አንጻር «ሌላ አይነት ግሎባላይዜሽን ያስፈልጋል» ብሎ ያምናል። የተሰ በሰቡትም «የአለም ዜጎች» ያለው አካሄድ አያዋጣም ከሚለው የጋራ እምነት ተነስተው አንድ አ ይነት የትኩረትና የአቅጣጫ ለውጥ እንደሚያስፈልግየሚያምኑ ተሳታፊዎች ነበሩ።

ዛሬ በአለማችን በግሎባላይዜሽን ሳቢያ ከፊታችን የተደቀኑትን ውስብስብ ችግሮች መጀመሪ ያ በአርእስት በአርእስት ለይቶ ሚድያ፣ፍትሃዊ አለም አቀፍ የንግድ ስርአት፣ በድሃ አገሮች ላይ የተጫነው እዳና የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ጥያቄ፣ ኢኮሎጂ፣ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር፣ እርሻና የህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የመመገብ መብት፣ ዘላቂነትያለው ተፈጥሮን የማያወድም የ ኢኮኖሚ እድገት፣ መንግስትና ልማት፣ የተሻሻሉ ዘሮች(ጀነቲካሊ ሞዲፋይድ ኦርጋኒዝምስ) ጥያቄ ና በመሳሰሉት አርእስቶች በሃያ ዎርክሾፖች የሁለት ቀናት ውይይት ተካሂዱዋል።

በሁለተኛ ደረጃ እነዚህን አርእስቶች አሁን ደግሞ ሁሉም ከሙያው አንጻር እንዲወያይባቸው በማሰብ እንደገና ሌሎች ሃያ «የሙያ ወርክሾፖች» ተቁዋቁመው የሁለት ቀናት ውይይት ተካሄደባቸው። በዚህ መሰረት አርቲስቶች፣ ጋዜጠኞች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ ነጋዴዎችና የኢንዱስትሪ ወሪዎች፣ መለዮ ለባሾች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ ባለአክስዮኖች፣ ገበሬዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ወዘተ በየሙያቸው ግሎባላይዜሽን ስላስከተላቸው ችግሮችና ስለመፍትሄ ሃሳቦች ተወያይተዋል።

ይህ ከተደረገ በሁዋላ ደግሞ ግሎባላይዜሽን በአለም የተለያዩ አካባቢዎች የሚያስከትላቸው መዘዞችም ሆኑ የሚጠይቃቸው አጸፋዎች ሙሉ በሙሉ አንድ አይነት ስላልሆኑ ተሳታፊዎች እንደመጡበት አካባቢ (የአፍሪካ ቀንድ፣ ደቡባዊ አፍሪካ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ምስራቅ አውሮፓ፣ ቻይና፣ ቅርብ ምስራቅ፣ ባልካንስ ወዘተ...) እየተባሉ በሃያ «የአካባቢ ዎርክሾፖች» ተሰማርተው ስለ አካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታና ችግሮች ተወያይተዋል።

በመጨረሻም የተሳታፊዎች በሙሉ ጠቅላላ ስብሰባ ተካሂዶ ለመጭዎቹ አመታት መመሪያ ሊሆን የሚችል «ቻርተር ኦፍ ሂውማን ሬስፖንሳቢሊቲ» በሚል ሰነድ ላይ ውይይት አካሂደዋል።

የሊሉ «የአለም ዜጎች ጉባኤ» ከመላው አለምና እጅግ የተሰበጣጠሩ የሙያ፣ የኑሮ፣ የቁዋንቁዋ፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የኑሮ ደረጃ ጀርባቸው የተለያዩ አራት መቶ ሰዎች ቢሳተፉበትም አራት መቶ ችግሮች ላይ ውይይት አልተካሄደበትም። በየትም ይሁን በየት አካባቢ ዛሬ አለማችንንና የአለምን ህዝቦች ወጥረው የያዙዋቸው ችግሮች እጅግ ከባድ ቢሆኑም በተወሰኑ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚሽከረከሩ የተወሰኑ የጋራ ችግሮች እንዳሉ አሳይቱዋል። አራት መቶ ተሳታፊዎች ቢኖሩም ሁሉም ቁልፍ በሆኑ የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ስምምነት ለመድረስ ችለዋል። ከሁሉም ከሁሉም በላይ ደግሞ ዛሬ በአለም ላይ የሰፈነው ስርአትለምድራችንም ለሰው ዘርም አደገኛ እንደሆነና ሊቀጥል እንደማይችል፣ ሊቀጥል አይችልም ሲባል ደግሞ ጭፍን ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን ሌላ ተአማኒነት ያለው ሊሰራ የሚችል፣ የአለም ህዝቦች በሙሉ ቁዋንቁዋቸውን፣ ሃይማኖታቸውን፤ ታሪካቸውን፣ የኑሮ ዘዴያቸውን፣እሴቶቻቸውንና፣ ባህሎቻቸውን፣ እንደያዙ ተከባብረው በጋራ ወደ ሰላምና ብልጽግና ሊወስዳቸው የሚችል የኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የማህበራዊ እድገት አማራጭ እንዳለ አሳይቱዋል። ለዚህ ነው ባርእስታችን ላይ አሁን ያለው አልሰራም ሌላ አለም ይቻላል ወይ? ብለን ላቀረብነው ጥያቄ አወን ሌላ አይነት አለም ይቻላል ብለን ባፍ ሙሉ መመለስ የምንችለው።

የቀስተደመና ሬድዮ የዝግጅት ክፍል በዚህ ጉባኤ ዝግጅት በተወሰነ ደረጃ የተሳተፈ እንደመሆኑ መጠን በየአርእስቱ ከጉባኤው ተሳታፊዎች የፈለቁት የጋራ ግንዛቤዎች ተጠናቅረው ለህትመት እንደበቁ ላድማጮቹ በአጭር በአጭሩ ለማስደመጥ ጥረት የሚያደርግመሆኑን እያስታወቀ የሃገራችን ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች፣ እንዲሁም በየመስኩ እውቀት ያዳበሩ ምሁራን በዚህ እጅግ ቁምነገር ባለበት ጉዳይ ያገባናል ብለው ውይይት እንዲከፍቱ ጥሪ ያደርግላቸዋል።